UW Medicine
UNIVERSITY OF WASHINGTON
MEDICAL CENTER

# ስለ ቀዶ ጥገና ልምድዎ

*በዋሽንግተን ዩኒቨርስቲ ሕክምና ማዕከል ውስጥ ለሚያደርጉት ቀዶ ጥገና ስለመዘጋጀት በዋሽንግተን ዩኒቨርስቲ ሕክምና ማዕከል -ምንትሌክ (UWMC) - Montlake*

ይህ ሥነ ጽሑፍ እና ከቀዶ ጥገና ሐኪምዎ እና ቅድመ-ማደንዘዣ( Pre-Anesthesia) ክሊኒክ ሰራተኞች ጋር ያደረጉት ቀጠሮ ለቀዶ ጥገና ዝግጁ እንዲሆኑ ይረዳዎታል ፡፡ ምን እንደሚከሰት እና ለምን እንደሆነ መረዳ ቱ አስፈላጊ ነው ፡፡ ደህንነቱ የተጠበቀ የቀዶ ጥገና ተሞክሮ እንዲኖርዎት ከእርስዎ ጋር ለመስራት በእርግጠኛ ቃል ገብተናል ፡፡

**እንዲሁም መመሪያዎችን ማንበብ እና የቅድመ-ቀዶ ጥገና ቪዲዮን በዋሽንግተን ሕክምና (UW Medicine) ድርጣቢያ ላይ ማየት ይችላሉ**
***www.uwmedicine.org/patient-care/how-to-prepare/uwmc***

ሥም:____________________________________________

የቀዶ ጥገና ቀን: ______________________________________

የቀዶ ጥገና ሐኪም:_____________________________________

የክሊኒክ ነርስ:________________________________________

ስልክ:_____________________________________________



*የዋሽንግተን ዩኒቨርስቲ ሕክምና ማዕከል -የምንትላኬ ካምፓስ በሲያትል ፣ ዋሽንግተን*

## ለቀዶ ጥገና ቀጠሮዎ የት እንደሚመዘገቡ

### በሥራ ቀናት ላሉ ቀዶ ጥገናዎች

- ❑ **2 ኛ ፎቅ የቀዶ ጥገና አገልግሎት መስጫ መቀበያ (Surgery Pavilion)**
  Surgery Pavilion, UWMC - Montlake campus

  1959 N.E. Pacific St., Seattle, WA 98195
- ❑ **2 ኛ ፎቅ የፓስፊክ መቀበያ (2nd Floor Pacific Admitting)**
  UWMC - Montlake campus

  1959 N.E. Pacific St., Seattle, WA 98195
- ❑ **የሮዝቬልት አምቡላቶሪ የቀዶ ጥገና ማዕከል መቀበያ**
  **Roosevelt Ambulatory Surgery Center Admitting**
  UWMC - Roosevelt, 1st floor

  4245 Roosevelt Way N.E., Seattle, WA 98105

### Saturday Surgeries የቅዳሜ ቀዶ ጥገናዎች

- ❑ **3 ኛ ፎቅ መመዝገቢያ አዳራሽ (3rd Floor Lobby Admitting)**
  UWMC - Montlake campus

  1959 N.E. Pacific St., Seattle, WA 98195

## የመድረሻ ሰዓት

የቅድመ-ሰመመን ክሊኒክ ሰራተኞች ከቀዶ ጥገናዎ 1 የስራ ቀን በፊት ከጠዋት 9:00 ሰዓት እስከ ከሰዓት3:00 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ይደውሉልዎታል ፡፡ የትኛው ቦታ እንደሚመዘገቡ ፣ በስንት ሰዓት እንደሚደርሱ እና ምን ይዘው እንደሚመጡ ይነግሩዎታል። ቀዶ ጥገናዎ ሰኞ ከሆነ ከዛ በፊት ያለው ዐርብ ይደውልሉዎታል። የቅድመ-ሰመመን ክሊኒክ ከቀዶ ጥገናዎ አንድ ቀን በፊት እስከ ከሰዓት 3:00 ሰዓት ድረስ ካልደወልልዎት በስልክ ቁጥር 206.598.6334 ይደውሉ።

## አስተርጓሚዎች

ከቀዶ ጥገናው በፊት እና በኋላ አስፈላጊ ከሆነ የዋሽንግተን ዩኒቨርስቲ ሕክምና ማዕከል(UWMC) እርስዎን የሚረዱ አስተርጓሚዎች አሉት ፡፡ አስተርጓሚ ከፈለጉ እባክዎን ለታካሚ እንክብካቤ አስተባባሪ ወይም ለቅድመ-ሰመመን ክሊኒክ ነርስ ይንገሩ ፡፡ ወይም ደግሞ ለአስተርጓሚ አገልግሎቶች ክፍል በ 206-598-4425 ይደውሉ እና አስተርጓሚ ይጠይቁ።

## የቅድመ-ቀዶ ጥገና ማረጋገጫ ዝርዝርዎ

ለቀዶ ጥገናዎ ዝግጁ መሆንዎን ለማረጋገጥ ይህንን የማረጋገጫ ዝርዝር ይጠቀሙ ፡፡ በተዘረዘረው ገጽ ላይ የእያንዳንዱ ነገር ዝርዝር ይፈልጉ ።

- ❑ **ከቀዶ ሕክምና ያደረጉ ቀን ከሆነ ወደ ቤትዎ የሚሄዱት ሀላፊነት የሚወስድ አዋቂ (አጃቢ) ሠው ወደ ቤትዎ የሚወስድዎት ሊኖርዎት ይገባል ፡፡ እራስዎ ነድተው ወይም በታክሲ ወይም አውቶቡስ ወደ ቤትዎ ለብቻዎ መሄድ አይችሉም ፡፡ አጃቢ ወይም ለሌላ እንደ ካቡላንስ (Cabulance)ዓይነት ተቀባይነት ያለው የትራንስፖርት አገልግሎት እቅድ ካላወጡ የቀዶ ጥገናዎን መሰረዝ ያስፈልገን ይሆናል** *፡፡ ገጽ 11 ን ይመልከቱ ፡፡*
- ❑ **ከሆስፒታል ከወጡ በኋላ በመጀመሪያዎቹ 24 ሰዓቶች ውስጥ ኃላፊነት የሚሰማው አዋቂ ሰው አብሮዎት እንዲሆን በጥብቅ እንመክራለን ፡፡** *ገጽ 11 ን ይመልከቱ ፡*

- ❑ **የቅድመ-ቀዶ ጥገና ጾም መመሪያዎችን ይከተሉ ::** *ገጽ 6 ን ይመልከቱ ::*
- ❑ **ገላዎን ስለመታጠብ እና ስለመላጨት የቅድመ-ቀዶ ጥገና መመሪያዎችን ይከተሉ** *:: □□ 7 ን ይመልከቱ ::*
- ❑ **በቀዶ ጥገናው ቀን መዋቢያ(ሜካፕ)፣ ዲዶራንት ፣ ሎሽን ፣ የፀጉር ምርቶችን ወይም ሽቶዎችን አይጠቀሙ ::** *ገጽ 7 ን ይመልከቱ □*
- ❑ **ሁሉንም የጌጣጌጥ እና አካል ላይ ተበስተው የገቡትን ጌጣጌጥ ያስወግዱ ::** *ገጽ 8 ን ይመልከቱ :*
- ❑ **የህክምና መድን (ኢንሹራንስ) ካርድዎን እና የፎቶ መታወቂያዎን ይዘው ይምጡ::** *ገጽ 8 ን ይመልከቱ*
- ❑ **የፋርማሲ መድን (ኢንሹራንስ) ካርድዎን ፣ የሠራተኛና ኢንዱስትሪ (L&I) መለያ ቁጥርዎን እና ካርድዎን እንዲሁም ሜዲኬር ወይም ሜዲኬይድ(Medicare or Medicaid ) መረጃዎን ካለዎት ይዘው ይምጡ ::** *ገጽ 8 ን ይመልከቱ ::*
- ❑ **የሚወስዷቸውን መድኃኒቶች ሁሉ ዝርዝር እና የእያንዳንዳቸውን መጠን ይዘው ይምጡ :: ይህ ቫይታሚኖችን ፣ ተጨማሪ ነገሮችን እና ያለ ማዘዣ የሚገዙትን ማንኛውንም ነገር ይጨምራል ::** *ገጽ 8 ን ይመልከቱ ::*
- ❑ **ከቀዶ ጥገናው በኋላ ለሚፈለጉ መድኃኒቶች ለማንኛውም ክፍያ የመክፈያ ዘዴ ይዘው ይምጡ ::** *ገጽ 8 ን ይመልከቱ ::*
  - የቀዶ ጥገና ማዕከሉ ጥሬ ገንዘብ ፣ ቼክ ወይም ክሬዲት ካርድ ይቀበላል ::
  - የሮዝቬልት አምቡላቶሪ (Roosevelt Ambulatory ) የቀዶ ጥገና ማዕከል ቪዛ ወይም ማስተርካርድ ብቻ ነው የሚቀበለው።
- ❑ **በሕክምና መዝገብዎ ውስጥ እንዲቀመጡ የጤና እንክብካቤ መመሪያዎን እና/ወይም ስለጤና እንክብካቤዎ ውክልና የሰጡባቸውን ወረቀቶች ግልባጭ ይዘው ይምጡ ::** ***ገጽ 8 ን ይመልከቱ ።***
- ❑ **□□□□□ □□□□□□ □□ □□ □□□□□ (CPAP )□□□□ □□□□□ □□□ □□□ □□□ □□** *□□ 8 □ □□□□□*
- ❑ **ጥበቃ የሚያስፈልጋቸውን ልጆች ይዘው አይምጡ:: ዕድሜያቸው 17 እና ከዚያ በታች የሆኑ ልጆች ወደ ሆስፒታል ከመጡ በማንኛውም ጊዜ በታካሚ መቆያ ክፍልም ሆነ በሌሎች የሆስፒታሉ አካባቢዎች ኃላፊነት ባለው ትልቅ ሰው ቁጥጥር ሊደረግባቸው ይገባል ::** *ገጽ 9 ን ተመልከት።*
- ❑ **መድኃኒቶችዎን ያስተካክሉ**

  ከቀዶ ጥገናዎ ከ ___ ቀናት በፊት እነዚህን መድሃኒቶች መውሰድ **ያቁሙ**

  ______________________________________________

  ______________________________________________

  □ቀዶ ጥገናው ቀን እነዚህን መድሃኒቶች **አይወስዱ፥**

  ______________________________________________

______________________________________________

የቀዶ ጥገናው ቀን እነዚህን መድኃኒቶች ከ 2 አውንስ (ከ 4 የሾርባ ማንኪያ) በማይበልጥ ውሃ ይውሰዱ ፡፡

______________________________________________

______________________________________________

ከቀዶ ጥገና ሐኪምዎ ጋር ስለመገናኘት

- ከቅድመ-ማደንዘዣ (Pre-Anesthesia) ክሊኒክ ቀጠሮዎ በፊት ከቀዶ ጥገና ሐኪምዎ ጋር በዋሽንግተን ዩኒቨርስቲ ሕክምና ማዕከል( UWMC) ልዩ ሕክምና ክሊኒክ ይገናኛሉ ፡፡ በዚህ ስብሰባ ላይ የቀዶ ጥገና ሀኪምዎ እና ሌሎች እንክብካቤ ሰጭዎችዎ
- የህክምና ታሪክዎን እና እቤት ስለሚወስዷቸው መድሃኒቶችን ይገመግማሉ
- አካላዊ ምርመራ ያድርጉ
- ስለ ቀዶ ጥገናው ከእርስዎ ጋር ይወያያሉ
- የፈቃድ (የስምምነት) ቅጽ ያስፈርሙዎታል

ከቀዶ ጥገናው በኋላ እንቅስቃሴዎ እንዴት ሊገደብ እንደሚችል እና እነዚህ ገደቦች ለምን ያህል ጊዜ እንደሚቆዩ የቀዶ ጥገና ሐኪምዎን ይጠይቁ ፡፡ በጥንቃቄ ምን ዓይነት እርዳታ እንደሚያስፈልግዎ ያስቡ እና ከቀዶ ጥገናው በፊት እርዳታውን ያዘጋጁ ፡፡ እንዴት ወደ መጸዳጃ ቤት እንደሚደርሱ ፣ ደረጃ መውጣት እና መውረድ ፣ ምግብዎን ማዘጋጀት እና ለራስዎ መንከባከብ ያሉ ነገሮች ላይ ይዘጋጁ ፡፡

## የቅድመ-ማደንዘዣ (Pre-Anesthesia) ክሊኒክ ቀጠሮዎት

ከቀዶ ጥገናዎ በፊት ስለ ጤናዎ መረጃ እንፈልጋለን ፡፡ ሐኪሞችዎ እንክብካቤዎን እና ማገገምዎን ሊያውኩ ስለሚችሉ ጉዳዮች ማወቅ አለባቸው።

ወደ ቅድመ-ማደንዘዣ (Pre-Anesthesia) ክሊኒክ ሲመጡ የሚከተሉትን ማምጣትዎን ያረጋግጡ፡-

- የሚወስዷቸውን ሁሉ መድሃኒቶች ዝርዝር እና የእያንዳንዳቸውን መጠን።
- በማንኛውም ሌላ ሆስፒታል ወይም ክሊኒክ ያደረጓቸውን የምርመራ ውጤቶች ፣ በተለይም የልብ ወይም የሳንባ ምርመራዎች ለምሳሌ ኤሌክትሮ ካርድዮግራም (ኢኬጂ)(EKG) ፣ የጭንቀት ምርመራ ፣ ኢኮካርዲዮግራም ወይም የሳንባ ሥራ ምርመራዎች ፡፡ የእነዚህን መዝገቦች (ሪኮርዶች) ግልባጭ በቀዶ ጥገና ፋይልዎት ውስጥ እናካትተዋለን ፡፡

እባክዎ ከሐኪምዎ ወይም ክሊኒክዎ የምርመራ ውጤቶችን ለማግኘት እርዳታ ከፈለጉ ይጠይቁን እኛም ልንረዳዎ እንችላለን ፡፡

በማደንዘዣ መድሐኒት ልዩ ባለሙያ የሆኑ ሐኪሞች የጤና ጥናትዎን ፣ የህክምና ታሪክዎን ፣ እቤት የሚወስዷቸውን መድሃኒት ዝርዝርዎን እና የምርመራ ውጤቶችዎን ይገመግማሉ ፡፡ ይህ መረጃ ለእርስዎ ምን ዓይነት ማደንዘዣ መድሐኒት በተሻለ እንደሚሠራ ለማወቅ ይረዳቸዋል ፡፡ እንደሚያደርጉት የቀዶ ጥገና ዓይነት የደም ምርመራዎች ፣ (ኢኬጂ)(EKG) ወይም ሌሎች ምርመራዎች ማድረግ ሊኖርብዎት ይችላል ፡፡

በዚህ ቀጠሮዎ ላይ የማደንዘዣ መዲሐኒት የሚሰጥዎትን ሐኪሞች ቡድን አያገኟቸውም ፡፡ የቀዶ ጥገናዎት ዕለት ያገኟቸዋል።

## ከቀዶ ጥገና በፊት ያሉ መድሃኒቶች

ለቀዶ ጥገና ሐኪምዎ እና ለቅድመ-ማደንዘዣ(Pre-Anesthesia) ክሊኒክ ሰራተኞች ምን ዓይነት መድሃኒቶች እንደሚወስዱ መንገርዎን ያረጋግጡ ፡፡ አንዳንዶቹን ከቀዶ ጥገናው በፊት ለአንድ ቀን ወይም ከዚያ በላይ መውሰድ ማቆም ያስፈልግዎ ይሆናል ፡፡

መውሰድዎን ለማቆም የሚያስፈልጉዎት አንዳንድ መድሃኒቶች

- የሚዋጡ የስኳር ህመም ክኒኖች እና ኢንሱሊን መድሃኒቶች
- ዎርፋሪን (ኮማዲን)Warfarin (Coumadin)
- ክሎፒዶግሬል (ፐላቪክስ) (Clopidorgel (Plavix)
- አስፐሪን እና ሌሎች መድሃኒቶች የደም መርጋት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ እንደ አይቢዩፕሮፌን (አድቪል ፣ ሞትሪን እና ሌሎች) እና ናፐሮክሲን (አሌቬ ፣ ናፐሮሲን እና ሌሎች)(ibuprofen (Advil, Motrin, and others) and naproxen (Aleve, Naprosyn) ያሉ
- የተወሰኑ የአመጋገብ መድኃኒቶች
- ከዕፅዋት የተቀመሙ መድኃኒቶች እና ተጨማሪ ድጋፍ ሰጪዎች

በቀዶ ጥገናው ጠዋት ላይ የትኛውን መድሃኒት መውሰድ እንደሚችሉ ሐኪምዎ ይነግርዎታል (ገጽ 3 እና 4 ን ይመልከቱ)።

## ማደንዘዣ

ምቾት እንዲኖርዎ በቀዶ ጥገናዎ ወቅት የማደንዘዣ መድሐኒት ሰጭዎች ቡድን ከእርስዎ ጋር ይሆናሉ። እንዲሁም እስትንፋስዎን ፣ የልብ ምትዎን  የደም ግፊትዎን እና ሊከሰቱ የሚችሉ ማንኛውንም የህክምና ጉዳዮች ይቆጣጠራሉ ፡፡

በቅድመ-ማደንዘዣ (Pre-Anesthesia) ክሊኒክ ቀጠሮዎ ጊዜ እንክብካቤ ሰጪዎችዎ ከሚቀጥሉት ማደንዘዣ ዓይነቶች 1 ወይም ከዚያ በላይ ስለመስጠት ሊያነጋግሩዎት ይችላሉ፡-

- **ጠቅላላ ማደንዘዣ**-እርስዎ ምንም አያውቁም (ተኝተዋል) እና ስለ ቀዶ ጥገናው ምንም ግንዛቤ አይኖርም ፡፡

- **የክልል ማደንዘዣ**-የማደንነዘዣ መድሃኒት በነርቭ ስብስብ ውስጥ ይወጋል፤ ስለሆነም የሰውነትዎ ሰፋ ያለው(አብዛኛው)ክፍል ስሜት አይሰማዎትም ፡፡ እንዲሁም ዘና ለማለት ወይም ለመተኛት እንዲረዳዎ መድሃኒት ሊሰጥዎ ይችላል።

- **ክትትል የሚደረግበት የማደንዘዣ እንክብካቤ** (ማክ-MAC) መድኃኒቶች በክንድዎ ውስጥ ባለው የደም ሥር በኩል ይሰጣሉ (በደም ሥሩ) ፡፡ ማስታገሻ (ዘና ለማለት የሚረዳ መድሃኒት) ሊሰጥዎት ይችላል ፣ ነገር ግን በቀዶ ህክምና ሂደቱ ወቅት ንቁ ሊሆኑ ይችላሉ ፡፡ እንዲሁም ማደንዘዣው ቀዶ ህክምና የሚከናወንበትን አካባቢ ብቻ የሚያደነዝዝ ሊሰጥዎት ይችላል። ፣ ይህም አሰራሩ ያደነዝዛል። በማክ (MAC)የሚሰጠው እንዲደብትዎት፣ በጣም እንዲያቀላፉ፣ ወይም በጥልቅ እንቅልፍ ውስጥ እንዲሆኑ ሊያደርጎት ይችላሉ ፡፡

እባክዎን ማናቸውም ልዩ ስጋቶች ካለዎት በቅድመ-ማደንዘዣ (Pre-Anesthesia) ቀጠሮዎ ወቅት ከማደንዘዣ ባለሙያው ጋር ለመነጋገር ከፈለጉ ለእንክብካቤ ሰጪዎ ይንገሩ ፡፡

## ከቀዶ ጥገናዎ በፊት

ከቀዶ ጥገናው በፊት ባለው ቀን እና ምሽት ዶክተርዎ አንጀት ለማፅዳት መመሪያ ካልሰጠዎት

በቀር በተለመደው ሁኔታ ይብሉ እና መድሃኒቶችዎን እንደተለመደው ይውሰዱ ፡፡

ከቀዶ ጥገና ቀንዎ በፊት ከእኩለ ሌሊት ጀምሮ *የጾም መመሪያዎቻችንን ይከተሉ*

## ስለ መጾም (ከቀዶ ጥገና በፊት ምግም ስለመብላት) መመሪያዎች

**ከቀዶ ጥገናዎ በፊት የጾም መመሪያዎቻችንን መከተል አለብዎት።** ለደህንነትዎ ሲባል የጾም መመሪያዎቻችንን ካልተከተሉ የቀዶ ጥገና ሕክምናዎን ቀጠሮ ወደ ሌላ ቀን ማስተላለፍ ያስፈልገን ይሆናል ፡፡

እነዚህ መመሪያዎች አስፈላጊ ናቸው ፡፡ በቀዶ ጥገና ወቅት የማስታወከዎ እና በሆድ ውስጥ ያሉትን ይዘቶች ወደ ሳንባዎችዎ የመግባት ዕድልዎን ዝቅ ያደርጋሉ ፡፡

አንዳንድ ሕመምተኞች ከቀዶ ጥገናው ዋዜማ ከእኩለ ሌሊት በኋላ ፈሳሽ መጠጣት ይችሉ ይሆናል ፡፡ ይህ በሚደረግልዎት የቀዶ ጥገና ዓይነት ላይ የተመሠረተ ነው ፡፡ እርስዎ መከተል ያለብዎትን መመሪያ የሕክምና ሰጨዎ ያብራራል።

ከቀዶ ጥገናው በፊት ስላለመብላት እና ስላለመጠጣት እነዚህን መመሪያዎች ይከተሉ፦

### ለሁሉም ሕመምተኞች

- ከእኩለ ሌሊት በኋላ ምግብ እንዳይበሉ
- ከእኩለ ሌሊት በኋላ አልኮል መጠጦችን አይጠጡ።
- **ከእኩለ ሌሊት በኋላ ግልፅ (በውስጣቸው ማየት የሚችሉባቸው)ፈሳሾችን እንዳይጠጡ ቢነገርዎት፦**
- ሐኪምዎ እንዳዘዘው መድሃኒቶችዎን በጠዋት ይውሰዱ ፡፡ ከ 2 አውንስ (ከ4 የሾርባ ማንኪያ) ባልበለጠ ውሃ ይውሰዷቸው

**ለቀዶ ጥገናዎ ክሊኒካላዊ እንክብካቤ እያመሩ ከሆኑ፦**

- የፖም ጭማቂዎን መቼ እንደሚጠጡ የቀዶ ጥገና ሐኪምዎን መመሪያዎች ይከተሉ። አብዛኛዎቹ ህመምተኞች ከእኩለ ሌሊት በፊት 8 አውንስ ይጠጣሉ እንዲሁም በዋሽንግተን ዩኒቨርስቲ ሕክምና ማዕከል (UWMC)የመኪና ማቆሚያ ጋራዥ ሲደርሱ 8 አውንስ ይጠጣሉ

**ከእኩለ ሌሊት በኋላ ግልፅ ፈሳሾችን (በውስጣቸው ማየት የሚቻልባቸውን)መጠጣት ይችላሉ ከተባሉ፦**

- እንደ ውሃ ያሉ ፈሳሾችን፤ ፖም ፣ ክራንቤሪ ወይም ሌሎች ንጹህ ጭማቂዎች(ፍራፍሬው የልለበት)፣ ጌቶራይድ; እና ሻይ ብቻውንመጠጣት ይችላሉ።
- የብርቱካን ጭማቂ ፣ ቡና ወይም ሻይ በክሬም ወይም በወተት ወይም ሌሎች ግልጽ ያልሆኑ (በውስጣቸው ማየት የማይቻልባቸውን ፈሳሾችን)**አይጠጡ** ፡፡
- ለቀዶ ጥገናዎ ከመድረስዎ ከ 2 ሰዓታት በፊት ጀምሮ ምንም ነገር እንዳይጠጡ ፡፡ በእነዚያ 2 ሰዓታት ውስጥ መድሃኒቶችን መውሰድ ከፈለጉ ከ 2 አውንስ (ከ4 የሾርባ ማንኪያ) ባልበለጠ ውሃ ይውሰዱ ፡፡

### በሲኤችጂ (CHG) ሳሙና ገላዎትን ይታጠቡ

**በቀዶ ጥገናው ዋዜማ እና የዕለቱ ለት ጠዋት ገላዎትን ይታጠቡ ፡፡**
*ክሎረክሳይዲን ግሉኮኔት Chlorhexidine gluconate* (ሲኤችጂ-CHG) በሚባለው ልዩ ሳሙና ይታጠቡ ፡፡

ሲኤችጂ (CHG)ሳሙናን በብዙ ትላልቅ የመድኃኒት መደብሮች መግዛት ይችላሉ ፡፡ የ 2% ወይም 4% (2 በመቶ ወይም 4 በመቶ)የሚለውን ፈሳሽ መጠቀም ይችላሉ ፡፡ የተለመደው የምርት ስሙ *ሂቢሌንስ* (*Hibiclens*) ነው ፤ ግን ሌላ ዓይነት የምርት ስም ያለውን ሊጠቀሙ ይችላሉ።

ገላዎትን በቀዶ ጥገናው ዋዜማ እና የዕለቱ ለት ጠዋት ለመታጠብ

1. ፊትዎን እና ፀጉርዎን መታጠብ ከፈለጉ መጀመሪያ መደበኛ ሳሙናዎን እና ሻምፑ በመጠቀም ይታጠቡ ፡፡ በሲኤችጂ (CHG)ሳሙና ፊትዎ ወይም ፀጉርዎ ላይ አይጠቀሙ
2. ፊትዎን እና ፀጉርዎን ካጠቡ በኋላ ከመታጠቢያው ይራቁ ወይም ውሃውን ይዝጉት ፡
3. በእርጥብ መታሻ ፎጣ ላይ የሲኤችጂ(CHG)ሳሙና አድርገው ከአንገትዎ እስከ እግር ጣቶችዎ ድረስ ይጠቀሙት ፡፡ መላው ሰውነትዎን ለማፅዳት በተለይም የቀዶ ጥገና የሚደረግበት የሰውነትዎ ክፍል እንደ አስፈላጊነቱ ተጨማሪ ሳሙና በመጨመር በደንብ ይታጠቡ ፡፡
4. የሲኤችጂ(CHG)ሳሙናው ለ 1 ሙሉ ደቂቃ በቆዳዎ ላይ እንዲቆይ ያድርጉ ፡፡ ከ 1 ደቂቃ በኋላ ውሃውን እንደገና ይክፈቱና ገላዎትን በደንብ ያለቅልቁ።
5. ቆዳዎን ዳብ ዳብ (ነካ ነካ)እያደረጉ በንጹህ ፎጣ ያድርቁ ፡፡ **ንጹህ** ልብሶችን ይልበሱ ፡፡
6. ጠዋት ገላዎን ከታጠቡ በኋላ መዋቢያ(ሜካፕ)፣ ዲዶራንት (ላብ መከላከያ) ፣ ሎሽን ፣ ማናቸውም የፀጉር ቅባት ውጤቶች ፣ ሽቶዎች ወይም ጌጣጌጦች **አይለብሱ** ፡፡

## ፂም (ፀጉር) ስለመላጨት

- ለኢንፌክሽን ተጋላጭነትን ለመቀነስ በየቀኑ የማይላጩትን ማንኛውንም የሰውነት ክፍል እንዳይላጩ ፡፡
- ቀዶ ጥገና የሚያደርጉበት አካባቢ በተለምዶ የሚላጩ ከሆነ ቀዶ ጥገናው ጠዋት ከመድረሱ በፊት ለ 2 ቀናት (48 ሰዓታት) ያንን ቦታ አይላጩ

## የመኪና ማቆሚያ እና አቅጣጫዎች

በሆስፒታሉ መኪና ማቆሚያ ማቆም ቅናሽ ዋጋ ይሰጥዎታል።፡ ለካርታዎች እና ለመኪና ማቆሚያ ቦታዎች አቅጣጫዎች ገጽ 14 እና 15 ን ይመልከቱ ፡፡ ለበለጠ መረጃ፡-

- ለዩኒቨርስቲ ዋሽንግተን(UW) ካምፓስ የመኪና ማቆሚያ እና ክፍያዎች በስልክ ቁጥር 206.685.1543 ይደውሉ
- የሆስፒታል ማቆሚያ በስልክ ቁጥር 206.598.5275 ይደውሉ
- ለሚነዱ ሰዎች አቅጣጫዎች www.washington.edu/admin/commuterservices/get_to_uw/visistor/index.php ድህረገፅ ይመልከቱ

## የእርስዎ ወደቤት ጉዞ

. ቀዶ ሕክምና በሚያደርጉበት በዚያውኑ ቀን ከሆስፒታል ለቀው ከሄዱ **መኪና መንዳት አይችሉም ወይም አውቶቡስ ወይም ታክሲን ብቻዎን ይዘው መሄድ አይችሉም ፡፡**

- ተጠያቂ የሚሆን አዋቂ (አጃቢ) ሠው ወደ ቤትዎ ወይም ወደ ማገገሚያ ተቋም የሚወስድዎት **መኖር አለበት** ፡፡ ይህ ሰው እርስዎ ገብተው መመቻቸትዎን እና ደህንነትዎ እና ምቾትዎ የተጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።
- ሲመጡ አጃቢዎ የማይገኝ ከሆነ ስማቸውን እና የስልክ ቁጥራቸውን እንጠይቃለን ፡፡ አጃቢ ከሌለዎት የቀዶ ጥገናዎ ሊሠረዝ ይችላል ፡፡
- አጃቢዎ ከሐኪም ቤት ሊወጡ ሲሉ ባለው 30 ደቂቃ ጊዜ ውስጥ በሆስፒታል ውስጥ መሆን አለበት ፡፡

## ለቀዶ ጥገና ወደ ሆስፒታል መምጣት

- መዋቢያ(ሜካፕ) ፣ ዲዶራንት (ላብ መከላከያ) ፣ ሎሽን ፣ ማናቸውም የፀጉር ቅባት ውጤቶች ፣ ሽቶዎች **እንዳይጠቀሙ**

- በቀላሉ ለማውለቅ የሚቻል  እና ቤት ውስጥ ለመልበስ ምቹ የሆነ ልቅ ልብስ ይልበሱ
- እባክዎን ውድ ዕቃዎችን (ከፍተኛ ዋጋ)ያላቸውን ይዘው አይምጡ ፡፡
- ሁሉንም አካል ላይ በመበሳት የገቡ እና ጌጣጌጦችን አውልቁ

## እርስዎ ምን ይዘው እንደሚመጡ

- የመድኃኒቶችዎን ዝርዝር እና የእያንዳንዳቸው መጠን። አምጡ ተብለው ካልተነገረዎት በስተቀር መድሃኒቶች አያምጡ፡፡
- የፎቶ መታወቂያ ፣የጤናዎ እና የመድኃኒትዎ መድን (ኢንሹራንስ) ካርዶች  ወደቤት ሲሄዱ ሊያስፈልግዎት ስለሚችል ማናቸውም መድሃኒቶች የድርሻዎን መክፈያ ዘዴ
- ሕክምና መዝገብዎ ውስጥ እንዲቀመጡ የጤና እንክብካቤ መመሪያዎን  እና/ወይም ስለጤና እንክብካቤዎ ውክልና የሰጡባቸውን ወረቀቶች ግልባጭ ይዘው ይምጡ ፡፡
- የሠራተኛና ኢንዱስትሪ (L&I) መለያ ቁጥርዎን
- የእንቅልፍ አፕኒያ (sleep apnea) ካለብዎ እና ማታ ማታ ሲተነፍሱ እንዲረዳዎ የሚጠቀሙት መሳሪያ ካለዎት
- ቀዶ ጥገናዎ እስኪጀመር ድረስ በመጠባበቅ ላይ እያሉ የሚያነቡት መጽሐፍ ወይም የሚሠሩት ፕሮጀክት (ዕቅድ) ካለ

## መድረስዎትን ያስመዝግቡ

በቀዶ ጥገናው ቀን በዚህ በራሪ ወረቀት ገጽ 2 ላይ ወደተመረጠው ቦታ ይምጡ ፡፡

ብዙውን ጊዜ ከቀዶ ጥገናው በፊት ከ 1½ እስከ 2 ሰዓታት ቀድመው እንዲመጡ እንጠይቃለን ፡፡ ይህ እርስዎን ለቀዶ ጥገና ለማዘጋጀት ጊዜ ይሰጠናል ፡፡ በዚህ ጊዜ፦

- ሕኪም ቤት መቀበያዎትን(የመግቢያዎት) ቅጾችን ይፈርማሉ ፡፡
- በጤንነትዎ ላይ ያሉ ማናቸውንም ለውጦች እናረጋግጣለን ፡፡
- የቀዶ ጥገና ሕክምናዎን መጀመሪያ ሰዓት ሊያውኩት ስለሚችሉ ማናቸውም ለውጦች እነግርዎታለን ፡፡

### ሴት ታካሚዎች

ከቀዶ ጥገናው በፊት ስለ ሽንት እርግዝና ምርመራ መረጃ ሊቀበሉ ይችላሉ ፡፡ ምርመራ ማድረግ ከፈለጉ ለነርስዎ ወይም ማደንዘዣ መድሃኒት ለሚሰጡት ሠራተኞች  ይንገሩ ፡፡

# ለቀዶ ጥገና ዝግጁ መሆን

ብዙ ሕመምተኞች ለቀዶ ጥገናቸው ለመዘጋጀት በቀዶ ጥገናው “ቅድመ ዝግጅት” አካባቢ ይሆናሉ ፡፡ የግልዎ በሆነ ቦታ የውስጥ  ሱሪዎችን ጨምሮ ልብሶችዎን እንዲያወልቁ እና ወደ ሆስፒታል ካባ ቀሚስ እንዲቀይሩ እንጠይቅዎታለን ፡፡

መነጽሮችን ፣ ዓይን ውስጥ የሚገቡ እንደመነጽር የሚያገለግሉ ሌንሶችን እና ለመስማት የሚያግዝ ጆሮ ላይ የሚደረጉ መሣሪያዎችን ማውለቅ ያስፈልግዎታል ፡፡ ሰው ሰራሽ የሚገባና የሚወጣ  ጥርስ (ዴንቸር)ካደረጉ እንዲያወልቁት ሊጠየቁ ይችላሉ ፡፡ እባክዎን የእነዚህን ዕቃዎች ማስቀመጫዎች  ካለዎት ይዘው ይምጡ ፡፡

በቀዶ ጥገናው ወቅት እርስዎን የሚንከባከቡትን ነርሶች ፣ የቀዶ ጥገና ሐኪሞች ቡድን እና ማደንዘዣ የሚሰጡዎቱን ቡድን ያገኛሉ ፡፡ ስለ እንክብካቤዎ ያለዎትን ማንኛውንም ጥያቄ ለመጠየቅ ይችላሉ ፡፡

በኢንፌክሽን የመያዝ ዕድልን ለመቀነስ ወደ ቀዶ ጥገና ክፍል እስኪገቡ ሲጠብቁ ሰውነትዎ እንዲሞቅ በሚሞቅ ብርድ ልብስ ይሸፈናሉ ፡፡ ካላገኙ የማሞቂያ ብርድ ልብስ ስጡኝ ብለው ይጠይቁ

## ለእርስዎ ድጋፍ ሰጪ ሰው

"በሚሰናዱበት" ጊዜ አንድ አዋቂ ሰው ድጋፍ ሰጪ ከእርስዎ ጋር መሆን ይችላል።

- እባክዎን ድጋፍ የሚሰጥዎት ሰው ጤናማ መሆኑን ያረጋግጡ ፡፡
- ድጋፍ የሚሰጥዎት ሰው አስፈላጊ ከሆነ ከሚሰናዱበት ክፍል እንዲወጣ ሊጠየቅ ይችላል ፡፡
- ወደ ቀዶ ሕክምና ሲወሰዱ ደጋፊዎ ሰው እንግዳ መቆያ ክፍል ውስጥ ሊጠብቅ ይችላል ፡፡ በሚጠብቁበት ጊዜ የሚያነቡትን ነገር ወይም ላፕቶፕ ኮምፒተር ወይም ሌላ የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያ እንዲጠቀሙት ማምጣት ይፈልጉ ይሆናል ፡፡ ገመድ አልባ የበይነመረብ (ኢንተርኔት-internet) አገልግሎት በአብዛኛዎቹ የሆስፒታሉ አካባቢዎች ይገኛል ፡፡
- እኛ የልጆች እንክብካቤ መስጠት አንችልም። ዕድሜያቸው 17 እና ከዚያ በታች የሆኑ ልጆች ወደ ሆስፒታል ከመጡ በማንኛውም ጊዜ በታካሚ መቆያ ክፍልም ሆነ በሌሎች የሆስፒታሉ አካባቢዎች ኃላፊነት ባለው ትልቅ ሰው ቁጥጥር ሊደረግባቸው ይገባል ፡፡

## ቀዶ ጥገና የሚደረግበት ቦታ ላይ ምልክት ማድረግ

ከፍተኛ ጥራት ያለው እና ደህንነቱ የተጠበቀ እንክብካቤን እንዲያገኙ ለማድረግ ቃል እንገባለን ፡፡ እዚህ በሚሆኑበት ጊዜ እርስዎ ወይም ቤተሰብዎ የሚከተሉትን የሚመስሉ ጥያቄዎች ይጠየቃሉ፡-

- *ሥምዎ ማን ይባላል?*
- *የተወለዱት መቼ ነው(ወር፣ቀን እና ዓ.ም.)?*
- *ምን ዓይነት ቀዶ ጥገና ነው የሚያደርጉት?*

እባክዎ በእነዚህ ጥያቄዎች አይደናገጡ ፡፡ ማንነትዎን እናውቃለን ፡፡ ለራስዎ ደህንነት ሲባል እነዚህን አንዳንድ ወይም ሁሉንም ጥያቄዎች ደጋግመን እንጠይቃለን

የቀዶ ጥገናውን ወይም የሕክምና ሂደት የሚደረግበትን ቦታዎ ለማረጋገጥ ዶክተርዎ የሕክምና መዝገብዎን ይመለከትና እና ከእርስዎ ወይም ከቤተሰብ አባል ጋር ይነጋገራል ፡፡ ብዙ ጊዜ ቀዶ ጥገና ወይም የሕክምና ሂደት ሲኖርዎ ሐኪምዎ ደህንነትዎን ለማረጋገጥ የቀዶ ጥገና የሚደረግበት ቦታ ላይ በብዕር ምልክት ያደርጋል።


የቀዶ ጥገና ቦታው ምልክት መደረግ ካለበት የቀዶ ጥገና ሀኪምዎ ቦታውን በስሙ ፊደሎች ምልክት ያደርግባቸዋል ፡፡ በሰውነትዎ በቀኝ ወይም በግራ በኩል የቀዶ ጥገና ወይም የሕክምና ሂደት የሚያደርጉ ከሆነ ልዩ ጥንቃቄ ይደረጋል ፡፡ **እባክዎን እራስዎን ምልክት አያድርጉ ወይም በሰውነትዎ ላይ ምንም ነገር አይፃፉ ፡፡**

የቀዶ ጥገናው ወይም የሕክምና ሂደቱ ቦታ ምልክት ማድረግ የማያስፈልገው ከሆነ ምን ዓይነት ቀዶ ጥገና ወይም ሕክምና ሂደት ሊያደርጉ እንደሆነ እንዲያረጋግጡ እንጠይቅዎታለን።

## መድሐኒትና ፈሳሽ መስጫዎችን ቱቦ (IV) ለማስገባት መጀመር

ቀዶ ጥገናዎ ከመጀመሩ በፊት በደም ቧንቧ መስመር ቱቦ (አይቪ-IV) እናስገባለን ፡፡ አይቪ (IV) በቀዶ ሕክምና ወቅት መድሐኒት እና ፈሳሽ እንዲሰጥዎ የሚያገለግል ትንሽ መርፌ እና ቀጭን ቱቦ ነው ፡፡ እንዲሁም ወደ ቀዶ ጥገና ከመግባትዎ በፊት ዘና ለማለት እንዲረዳዎ በአይቪ (IV) በኩል መድሃኒት ሊሰጥዎ ይችላል ፡፡

በመጀመሪያ አይቪው (IV) የሚገባበት ቦታ ቆዳዎ ላይ ማደንዘዛ መድኃኒትን እናደርጋለን ፡፡ ብዙ ጊዜ ፣ ይህ የሚሆነው በእጅዎ ወይም በክንድዎ ላይ ነው




*የቀዶ ጥገና ሐኪም ታካሚው ቀዶ ሕክምና የሚደረግበት ቦታ ላይ የራሱን ስም ሲጽፍ*

## ከቀዶ ጥገና በኋላ

### የማገገሚያ ክፍል

ከቀዶ ጥገናው በኋላ ወደ ማገገሚያ ክፍል ይወሰዳሉ ፡፡ የማገገሚያ ክፍሉ እንዲሁ ከማደንዘዣ በኋላ እንክብካቤ ክፍል (PACU) ተብሎ ይጠራል ፡፡

ልክ ከቀዶ ጥገናዎ በኋላ መጀመሪያ ቅድሚያ የምንሰጠው ነገር ለእርስዎ የሚፈልግዎትን እንክብካቤ መስጠት ነው ፡፡ ከማደንዘዣው እየነቁ ሲመጡ ደህንነትዎን እና እንደ አስፈላጊነቱ ለህመም ማስታገሻ እንደሚሰጥዎት ማረጋገጥ እንፈልጋለን ፡፡

አብዛኛዎቹ ህመምተኞች ከቀዶ ጥገናው በኋላ ከ 1 እስከ 2 ሰዓታት ውስጥ በማገገሚያ ክፍል ውስጥ ይሆናሉ ፡፡

### ጠያቂዎች

ከቀዶ ጥገናው በኋላ ወዲያውኑ የሚያስፈልግዎትን እንክብካቤ ካደረግን በኋላ ጠያቂዎችን መቀበል እንደሚችሉ ለቤተሰብዎች እንነግራቸዋለን ፡፡

- ከፈለጉ ብዙ ጊዜ የሚወዷቸው ሰዎች በማደንዘዣ በኋላ እንክብካቤ ክፍል (PACU ውስጥ ሊጠይቁዎት ይችላሉ። ከማደንዘዣ በኋላ እንክብካቤ ክፍል (PACU)ያለው አካባቢ ውስን ቦታ ነው ፤ ስለሆነም በአንድ ጊዜ አንድ አዋቂ የሆነ ሰው ብቻ ሊጠይቅዎት ይችላል ፡፡
- ሁሉም ጠያቂዎች ጤናማ የሆኑ  እንዲሆኑ እንጠይቃለን ፡፡ ኢንፌክሽን የለው ጠያቂ “ጉንፋን” እንኳን ቢሆን ፣ በማገገምዎ ወይም በሕክምናዎ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል።
- *ከቀዶ ጥገናው በኋላ ወደ አንዱ የኦንኮሎጂ (oncology) ክፍሎቻችን የሚገቡ ከሆነ፡-* ሁሉም ጠያቂዎች ወደ ክፍሉ ፎቅ ሲደርሱ ጤንነትን ማጣሪያ ግምገማ እናደርጋለን ፡፡ የበሽታ ምልክቶች ካላቸው ፤ ደህና ሲሆኑ ተመልሰው እንዲመጡ ልንጠይቃቸው እንችላለን ፡፡

### ታካሚውን መከታተል

ከቀዶ ጥገና እያገገሙ እያሉ ነርስዎ አተነፋፈስዎን ፣ የልብ ምትዎን እና የደም ግፊትዎን ቶሎ ቶሎ ይለኩዎታል፡ ፡ነርስዎ  የሚሰማዎትን ማንኛውም የማቅለሽለሽ  ወይም ሕመም ስሜት ካለዎት ይረዱዎታል። ለእርስዎ ምቾት መኖሩ አስፈላጊ ነው ፡፡

### ሕመምን መቆጣጠር

ሕመምዎ በጣም ከመባሱ በፊት ነርስዎን የህመም ማስታገሻ መድሃኒት መጠየቅዎን ያረጋግጡ ፡፡ ነርስዎ ህመምዎን ከ 0 እስከ 10 ባለው መጠን እንዲመዝኑ ይጠይቅዎታል ፤ 0 ምንም ሕመም የሌለበት እና 10 ደግሞ በጣም የከፋ ህመም ነው ፡፡ የሕመም ማስታገሻ፡-

- በአፍ (ክኒኖች ፣ እንክብል ወይም ፈሳሽ)
- በአይቪ (IV)በደም ቧንቧዎ የሚገባ መድሃኒት

በሆስፒታል ውስጥ የሚያድሩ ከሆነ በተጨማሪ እነዚህ ሊሰጥዎት ይችላሉ፡-

- በጀርባዎ ውስጥ በትንሽ ቱቦ በኩል የሚሰጥ የህመም መድሃኒት (epidural)
- ሕመምተኛው ራሱ የሚቆጣጠረው የሕመም ማስታገሻ ፒሲኤ (PCA)



*በፒሲኤ (PCA) አማካኝነት የሚወስዱትን የሕመም ማስታገሻ መድሃኒት መጠን እራስዎ ይቆጣጠራሉ ።*

**ሕመምተኛው ራሱ ስለሚቆጣጠረው የሕመም ማስታገሻ**

ፒሲኤ መሳሪያ( በሕመምተኛው ቁጥጥር የሚደረግ የህመም ማስታገሻ) አንዴ ቁልፍን ሲጫኑት (ሲገፉ) በአይቪ( IV)በደም ቧንቧዎ ውስጥ የህመም ማስታገሻ መድሃኒት መጠን ያስገባል፡፡ ፒሲኤ(PCA)ሲጠመቁ ነርስ መጠበቅ የለብዎትም ፡፡ በሕመም ማስታገሻዎች ላይ ቁጥጥር ያለዎት እርስዎ ብቻ ነዎት።

የእርስዎ ሐኪሞች ለእርስዎ በጣም ጥሩውን የመድኃኒት መጠን ያዝዛሉ። ፒሲኤን (PCA) እንደ መመሪያው የሚጠቀሙ ከሆነ ለእነዚህ መድኃኒቶች ሱስ **አይዝዎትም** ፡፡

**ማስጠንቀቂያ** ▯ ለደህንነትዎ ሲባል **እርስዎ ብቻ** ነዎት ፒሲኤ(PCA) ላይ ያለውን ቁልፍ መጫን ያለብዎት፡፡ ጠያቂዎችዎ የፒሲኤ(PCA) ቁልፉን እንዲጫኑ አይፍቀዱ ፡፡

## ቀዶ ጥገና ያደረጉበት ቀን ከሐክም ቤት ከወጡ

ከቀዶ ጥገናዎ ጋር በተመሳሳይ ቀን ከሆስፒታል ከወጡ እና ማስታገሻ ወይም ማደንዘዣ ከተሰጥዎት፡-

- ከቀዶ ጥገናው ወደ ቤትዎ ወይም የሚያገግሙበትም ቦታ የሚወስድዎት ሀላፊነት የሚሰማው አዋቂ አጃቢ ሰው **መኖር** አለበት ፡፡
- እርስዎ መንዳት **አይችሉም** ፡፡
- ለብቻዎ በታክሲ ወይም በአውቶቡስ መሄድ **አይችሉም** ፡፡

### ለመጀመሪያዎቹ 24 ሰዓታት

- ወደቤት እንዲሄዱ ከተለቀቁ በኃላ ኃላፊነት ያለው አዋቂ ሰው ለ 24 ሰዓታት ከእርስዎ ጋር እንዲቆይ በጥብቅ እንመክራለን ፡፡ ይህ አዋቂ ሰው በቤትዎ ወይም በማገገሚያዎ ቦታ እርስዎን መንከባከብ መቻል አለበት ፡፡ ይህም ለደህንነትዎ ከቀዶ ጥገናው በኋላ ማንኛውም ችግር ቢገጥምዎት እና ተጨማሪ እንክብካቤ ካስፈለግዎት ነው ፡፡ **ይህንን ምክር ላለመከተል ከመረጡ የዋሽንግተን ዩኒቨርስቲ ሕክምና ማዕከል(UWMC) ለደህንነትዎ ኃላፊነት የለውም ፡፡**
- ከቀዶ ጥገናው በኋላ የተወሰነ ህመም ምናልባትም የማቅለሽለሽ ስሜት ሊኖርብዎት ይችላል ፡፡ እንዲሁም ቀሪውን ቀኑን እንቅልፍ እልቅልፍ ሊልዎትይችላል።
- ማደንዘዣ መድሐኒት ከወሰዱ በኋላ ለ 24 ሰዓቶች ፤ **ማድረግ የሌለብዎት**
  - መንዳት
  - አልኮል መጠጥ መጠጣት
  - ለብቻ መጓዝ
  - መሳሪያዎች መጠቀም
  - ማንኛውንም ህጋዊ ወረቀቶች መፈረም
  - ለልጆች ፣ ለቤት እንስሳት ፣ ወይም እንክብካቤ ለሚፈልግ አዋቂ ሰው ሃላፊነት መውሰድ
- ከሆስፒታል ከመውጣትዎ በፊት የሚከተሉትን እንሰጥዎታለን፡-
  - እቤት ውስጥ እራስዎን እንዴት እንደሚንከባከቡ መረጃ።
  - የክትትል ሕክምና ቀጠሮዎትን ለማስያዝ የሚደውሉበት ስልክ ቁጥር ፤ ይህም አስቀድሞ ካልተያዘልዎት።

## ከቀዶ ጥገና በኋላ በሆስፒታል ውስጥ የሚያድሩ ከሆነ

- የሆስፒታል ካባ ቀሚስ (የሌሊት ልብስ) መልበስ ያስፈልግዎት ይሆናል ።።
- ደህንነትዎን ስንጠብቅ ትሁትነትዎን(ዓይን አፋርነትዎን)/ልከኝነትዎን ለመጠበቅ የምንችለውን ሁሉ እናደርጋለን ፡፡ ደህንነትዎ የመጀመሪያ ቅድሚያ የምንሰጠው ጉዳይ ነው ፡፡
- አልጋ ላይ ሳሉ በዝቅተኛ እግሮችዎ ክፍል ላይ በየተወሰነ ጊዜ ጭምቅ ጭምቅ የሚያደርጉ (SCD- *sequential compression devices* ) ሊደረግልዎት ይችላል ፡፡ እነዚህ እግርዎት ላይ የሚደረጉት የደም መርጋትን ለመከላከል ይረዳሉ



*ኤስሲዲ(SCDs)ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተነፉ በእግርዎት ውስጥ የደም ዝውውርን ይረዳሉ*

- እንዳይወድቁ ለማድረግ የሚከተሉትን ልንጠቀም እንችላለን፡-
  - ከአልጋዎ ሊወርዱ ሲሉ የሚነግረን ማስታወቂያ/ማስጠንቀቂያ
  - በአልጋዎ አጠገብ ወለል ላይ ያሉ ምንጣፎች
  - ከአልጋ ሲነሱ እና ሲራመዱ ሲሉ በወገብዎ ላይ ቀበቶ ማሰር
  - የሽንት ቤት ወይም የኮሞድ (አልጋ አጠገብ የሚሆን መፀዳጃ-commode) ሲጠቀሙ አንድ ሰራተኛ በአቅራቢያው ይሆናል
- ነገሮችን በራስዎ የማድረግ ችሎታዎ ከቀን ወደ ቀን ሊለወጥ ይችላል። ይህ ማለት የእርስዎ ደህንነት ለመጠበቅ እኛ የምናደርጋቸውን ነገሮች መለወጥ ያስፈልገን ይሆናል ማለት ነው ፡፡
- ከቱቦዎች እና መሳሪዎች ጋር የተገናኙ ሊሆኑ ይችላሉ።
- ሠራተኞቹ ምን እንደሚሰማዎት በቀን ውስጥ ብዙ ጊዜ ይጠይቁዎታል
- ምርመራዎች ውስጥ እንዲሳተፉ እንጠይቅዎታለን ፡፡

### የመውደቅ አደጋ/ዕድል

ሆስፒታል ውስጥ እያሉ የመውደቅ ዕድልዎ ከፍ ያለ ነው ፡፡ የዚህም ምክንያት:

- አዲስ ቦታ ላይ ስላሉ
- በጤንነትዎ ወይም በሕመምዎ ላይ ባሉ ለውጦች ደካማ እና ደክመው ይሆናል ፡፡
- ከቀዶ ጥገና በኋላ ወይም በሕመምዎ ምክንያት ማዞር ፣ ኸው ማለት ወይም ግራ መጋባት ሊሰማዎት ይችላል ፡፡

- አንዳንድ መድሃኒቶች በግልፅ የማሰብ ችሎታዎን ሊያውኩ ይችላሉ ፡፡
- አንዳንድ መድሃኒቶች አስቸኳይ የመሽናት ፍላጎት ሊያስከትሉ ይችላሉ (ሽንት) ፡፡
- የመታጠቢያዎ ልምዶችዎ በቤት ውስጥ ካሉበት ሁኔታ ይልቅ በሆስፒታሉ ውስጥ የተለዩ ናቸው
- አንዳንድ መድሃኒቶች በጡንቻዎት ጥንካሬ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ ፡፡
- ያበጡ እግሮች ይኖርዎት ይሆናል ፡፡
- ከቀዶ ጥገናው በኋላ እግሮችዎን በቀስታ ወይም እየጎተቱ ሊያንቀሳቅሱት ይችሉ ይሆናል ፡፡
- ከቤት ውጭ በደንብ መተኛት አይችሉ ይሆናል
- ቱቦዎች እና መሣሪያዎች በቀላሉ ለመንቀሳቀስ እንቅፋት ሊሆኑ ይችላሉ ፡፡

ሆስፒታል ውስጥ በሚቆዩበት ጊዜ እንዳይወድቁ እንዴት እንደምንረዳዎ በተመለከተ ጥያቄ ወይም የሚያሳስብዎት ነገር ካለ እባክዎን ነርሶችዎን ይጠይቁ።

## ጠቃሚ የስልክ ቁጥሮች

እነዚህ የስልክ ቁጥሮች ጠቃሚ ሆነው ሊያገኟቸው ይችሉ ይሆናል ፡፡ በሆስፒታሉ ውስጥ ያለ ስልክ የሚጠቀሙ ከሆነ በ 598 የሚጀምሩትን የመጨረሻዎቹን 5 አሃዞች ብቻ ይጫኑ (ለምሳሌ ከሆስፒታል ስልክ የተኝቶ ታካሚ ምዝገባ ክፍል ከፈለጉ 8-4310 ን ይጫኑ)

**ምዝገባ**........ 206.598.4310

**ሂሳቦች**

የፋይናንስ ምክር ........ 206.598.4320
የዶክተር ክፍያዎች (UW ሐኪሞች) ........ 206.543.8606
የዋሽንግተን ዩኒቨርስቲ ሕክምና ማዕከል (UWMC) የሂሳብ አከፋፈል 206.598.1950

**የአስቸኳይ ህክምና አገልግሎት**
(ድንገተኛ ክፍል ወይም ድ.ክ (ER)........ 206.598.4000

**የጤና መረጃ ግብዐት ማዕከል** ........ 206.598.7960

**የትርጉም አገልግሎት ቢሮ** ........ 206.598.4425
*TTY (መስማት ለሚሳናቸው)*........ 800.833.6384

**የጠፋ እና የተገኘ (ዕቃ መጠየቂያ)** ........ 206.598.4909

**ቀዶ ጥገና ክፍል**........ 206.598.4270

**የታካሚ ግንኙነት**........ 206.598.8382

**ፓቪሊዮን (Pavilion) የቀዶ ጥገና ማዕከል**........ 206.598.4214

**ቅድመ ማደንዘዣ ክሊኒክ**........ 206.598.5053

**የሩዝቬልት አምቡላተር የቀዶ ጥገና ማዕከል ( Roosevelt Ambulatory Surgery Center)** ........ 206.598.0900

**ማህበራዊ ሥራ እና እንክብካቤ ማስተባበር(Social Work and Care Coordination)**

**የቤት አገልግሎች** ........ 206.598.4170

ከቀዶ ጥገናው በኋላ ጥያቄዎች ወይም ስጋቶች ካሉዎት የቀዶ ጥገና ክሊኒክዎ ለመደወል ቁጥሮች ይሰጥዎት ይሆናል

## ቦታዎችን እና የመኪና ማቆሚያ


### የዋሽንግተን ዩኒቨርስቲ ሕክምና ማዕከል- ሞንትሌክ (UWMC – Montlake)

የዋሽንግተን ዩኒቨርስቲ ሕክምና ማዕከል- ሞንትሌክ (UWMC - Montlake ) በዋሽንግተን ዩኒቨርስቲ (UW) ካምፓስ በስተደቡብ መጨረሻ ላይ ይገኛል ፡፡ አድራሻው 1959 N.E. Pacific St Seattle ከእነዚህ ጋራዦች አንዱ ጋ ማቆም ይችላሉ፡-

- **Triangle Parking Garage** (across N.E. Pacific St. from the hospital) ትራያንግል የመኪና ማቆሚያ ጋራዥ (ከሆስፒታሉ ማዶ/ፊት ለፊት ፓስፊክ መንገድ አቋርጠው)
- **Surgery Pavilion Parking Garage** (at the east end of the hospital) ፓቪዮን የቀዶ ጥገና የመኪና ማቆሚያ ጋራዥ (በሆስፒታሉ በስተምሥራቅ መጨረሻ)

### የዋሽንግተን ዩኒቨርስቲ ሕክምና ማዕከል- ሩዝቬልት (UWMC - Roosevelt)

የዋሽንግተን ዩኒቨርስቲ ሕክምና ማዕከል- ሩዝቬልት( UWMC – Roosevelt) የሚገኘው ከዋሽንግተን ዩኒቨርስቲ ሕክምና ማዕከል- ሞንትሌክ (UWMC – Montlake) በሰሜን ምዕራብ 1 ማይል ያህል ርቀት በ4245 Roosevelt Way N.E., Seattle ነው ፡፡ የመኪና ማቆሚያ ጋራዡ ከሕንፃው ይገኛል።




*ኮከቦቹ ወደ ትሪያንግል ጋራዥ እና የፓቪሊዮን ማቆሚያ ጋራዥ መግቢያዎችን ያሳያሉ ፡፡*

## ለአሽከርካሪዎች አቅጣጫ መግለጫ

**የዋሽንግተን ዩኒቨርስቲ ሕክምና ማዕከል-ሞንትሌክ ካምፓስ (UWMC - Montlake Campus)** 1959 N.E. Pacific St., Seattle, WA 98195 ለመሄድ

- ከአይ 5 (ከኢንተር-ኢስቴት 5-I5)
  - ወደ ምስራቅ የሚወስደውን መውጫ 168ቢ (ቤሌቭው፤ ስቴት መስመር 520) ይውሰዱ።
  - ሞንትሌክ ቡሎቫርድ መውጫን ይውሰዱ።
  - የዋሽንግተን ዩኒቨርስቲ ሕክምና ማዕከል የሚለውን ምልክት ይከተሉ

- ከ405(ከኢንተር-ኢስቴት 405)
  - መውጫ 14ን ይዘው (ወደ ሲያትል ስቴት መስመር 520 በኩል) ወደ ምዕራብ ያምሩ።
  - ሞንትሌክ ቡሎቫርድ መውጫን ይውሰዱ።
  - የዋሽንግተን ዩኒቨርስቲ ሕክምና ማዕከል የሚለውን ምልክት ይከተሉ

**የዋሽንግተን ዩኒቨርስቲ ሕክምና ማዕከል- ሩዝቬልት(UWMC – Roosevelt)**
4245 Roosevelt Way N.E., Seattle, WA 98105 ለመሄድ

- ከአይ 5 (ከኢንተር-ኢስቴት 5-I5)
  - ኖርዝ ኢስት 45 ኛው መንገድ መውጫ (መውጫ 169)ን ይውሰዱ እና ኖርዝ ኢስት 45 ኛው ላይ ወደ ምስራቅ በማምራት ይሂዱ
  - ወደ ሩዝቬልት ዌይ ኖርዝ ኢስት ወደ ቀኝ በኩል ወደ ደቡብ ይታጠፉ እና 2½ ብሎኮችን ይሂዱ
  - የዋሽንግተን ዩኒቨርስቲ ሕክምና ማዕከል- ሩዝቬልት በቀኝ በኩል ይገኛል □□



የዋሽንግተን ዩኒቨርስቲ ሕክምና ማዕከል- ምንትሌክ (UWMC-Montlake) ካምፓስ ከኢንተርስቴት 5 (አይ 5)በምስራቅ እና ከስቴት መስመር 520 በስተ ሰሜን ይገኛል




## Questions?

የእኛን ምርጥ እንክብካቤ እንድንሰጥዎ ከእርስዎ ጋር አጋር መሆን እንፈልጋለን ። በእንክብካቤቸው የሚሳተፉ ታካሚዎች የተሻሉ ውጤቶች እና አነስተኛ ችግሮች ነው የሚኖራቸው ።

ጥያቄዎችዎ አስፈላጊ ናቸው ። ስለሚሰጥዎት እንክብካቤ የሚኖርዎትን ማንኛውንም ጥያቄ ተንከባካቢዎን ይጠይቁ ። የሚያሳስብዎት ነገር ካለ ለሠራተኛ አባል ይንገሩ ወይም ለዋሽንግተን ሕክምና ማዕከል የሕመምተኛ ግንኙነት በስልክ ቁጥር


© University of Washington Medical Center


Published PFES: 2003, 2010, 2013, 2015, 2016, 2017, 2018, 2019, 2020
Clinician Review: 07/2020
AMHARIC translation by UWMC Interpreter Services
Reprints on Health Online: https://healthonline.washington.edu

UW Medicine
UNIVERSITY OF WASHINGTON
MEDICAL CENTER

# About Your Surgery Experience

*Getting ready for your surgery at UW Medical Center (UWMC) - Montlake*

This handout and your visit with your surgeon and Pre-Anesthesia Clinic staff will help you get ready for surgery. It is important that you understand what will happen and why. We are committed to working with you for a safe surgery experience.

**You can also read instructions and watch a pre-surgery video on the UW Medicine website: *www.uwmedicine.org/patient-care/how-to-prepare/uwmc***

Name: ____________________________________________________________

Date of Surgery: ____________________________________________________

Surgeon: __________________________________________________________

Clinic Nurse: ______________________________________________________

Phone: ____________________________________________________________



*UW Medical Center - Montlake campus in Seattle, Washington*

## Where to Check in for Your Surgery

### Weekday Surgeries

- ❑ **2nd Floor Surgery Pavilion Admitting**
  Surgery Pavilion, UWMC - Montlake campus
  1959 N.E. Pacific St., Seattle, WA 98195
- ❑ **2nd Floor Pacific Admitting**
  UWMC - Montlake campus
  1959 N.E. Pacific St., Seattle, WA 98195
- ❑ **Roosevelt Ambulatory Surgery Center Admitting**
  UWMC - Roosevelt, 1st floor
  4245 Roosevelt Way N.E., Seattle, WA 98105

### Saturday Surgeries

- ❑ **3rd Floor Lobby Admitting**
  UWMC - Montlake campus
  1959 N.E. Pacific St., Seattle, WA 98195

## Arrival Time

Pre-Anesthesia Clinic staff will call you 1 business day before your surgery, between 9 a.m. and 3 p.m. They will tell you which admitting location to use, what time to arrive, and what to bring with you. If your surgery is on a Monday, they will call you the Friday before.

If you have not received this call from the Pre-Anesthesia Clinic by 3 p.m. the day before your surgery, call **206.598.6334**.

## Interpreters

UWMC has interpreters to help you, if needed, before and after surgery. Please tell the patient care coordinator or Pre-Anesthesia Clinic nurse if you want an interpreter. Or, call Interpreter Services at 206.598.4425 and ask for an interpreter.

## Your Pre-Surgery Checklist

Use this checklist to make sure you are ready for your surgery. Find details for each item on the page listed.

- ❑ **If you will be going home the same day as your surgery, you must have a responsible adult (*escort*) drive you home. You cannot drive yourself home or take a taxi or a bus by yourself. If you have not made plans for an escort or other approved transportation such as Cabulance, we may need to cancel your surgery.** *See page 11.*

- ❑ **We strongly advise that you have a responsible adult stay with you the first 24 hours after you leave the hospital.** *See page 11.*
- ❑ **Follow your pre-surgery fasting guidelines.** *See page 6.*
- ❑ **Follow your pre-surgery shower and shaving instructions.** *See page 7.*
- ❑ **Do not use makeup, deodorant, lotions, hair products, or fragrances on the day of surgery.** *See page 7.*
- ❑ **Remove all jewelry and body piercings.** *See page 8.*
- ❑ **Bring your medical insurance card and a photo ID with you.** *See page 8.*
- ❑ **Bring your pharmacy insurance card, Labor and Industry (L&I) claim number and card, and your Medicare or Medicaid information, if you have them.** *See page 8.*
- ❑ **Bring a list of all the medicines you take, and the doses of each one. This includes vitamins, supplements, and anything else you buy without a prescription.** See page 8.
- ❑ **Bring a method of payment for any co-pays for medicines needed after surgery.** *See page 8.*
  - Pavilion Surgery Center accepts cash, check, or credit card.
  - Roosevelt Ambulatory Surgery Center accepts only Visa or Mastercard.
- ❑ **Bring a copy of your healthcare directive and/or durable power of attorney for healthcare so they can be placed in your medical record.** *See page 8.*
- ❑ **If you use a CPAP machine at night to help you breathe, bring it with you.** *See page 8.*
- ❑ **Do not bring unattended children with you. If children age 17 and under come to the hospital, they must be supervised by a responsible adult at all times, both in the waiting room and in other areas of the hospital.** *See page 9.*
- ❑ **Adjust your medicines:**

  **Stop** taking these medicines _____ days before your surgery:

  ________________________________________

  ________________________________________


Pre-Anesthesia Clinic | UWMC Montlake Campus | Box 358119
1959 N.E. Pacific St., Seattle, WA 98195 | 206.598.6334

Do **NOT** take these medicines on the day of your surgery:

________________________________________________

________________________________________________

**Take** these medicines on the day of your surgery with no more than 2 ounces (4 tablespoons) of water:

________________________________________________

________________________________________________

## Meeting with Your Surgeon

Before your visit to the Pre-Anesthesia Clinic, you will meet with your surgeon in a UWMC specialty clinic. At this meeting, your surgeon and other care providers will:

- Review your medical history and home medicines
- Do a physical exam
- Talk with you about the surgery
- Have you sign a consent form

Ask your surgeon how your activity might be limited after surgery and how long these limits will last. Think carefully about what help you will need and arrange for this help before your surgery. Work out things like how you will get to the bathroom, go up and down stairs, prepare your meals, and care for yourself.

## Your Pre-Anesthesia Clinic Visit

We need information about your health **before** your surgery. Your doctors need to know about issues that may affect your care and recovery.

When you come to the Pre-Anesthesia Clinic, be sure to bring:

- A list of all the medicines you take and the doses of each one.
- **The results of tests you have had at any other hospital or clinic**, especially heart or lung tests such as an electrocardiogram (EKG), stress test, echocardiogram, or pulmonary function tests. We will include copies of these records in your surgical packet.

If you need help getting test results from your doctor or clinic, please ask us and we can help you.

Providers who are experts in anesthesia will review your health survey, medical history, home medicine list, and test results. This information

will help them know what kind of anesthesia will work best for you. You may also need to have blood tests, an EKG, or other tests, depending on your type of surgery.

You will not meet your anesthesia team at this visit. You will meet them the day of your surgery.

## Medicines Before Surgery

Be sure to tell your surgeon and Pre-Anesthesia Clinic staff what medicines you are taking. You may need to stop taking some of them for a day or more before your surgery.

Some medicines you may need to stop taking are:

- Oral diabetes medicines and insulin
- Warfarin (Coumadin)
- Clopidogrel (Plavix)
- Aspirin and other medicines that affect blood clotting, such as ibuprofen (Advil, Motrin, and others) and naproxen (Aleve, Naprosyn, and others)
- Certain diet medicines
- Herbal remedies and supplements

A provider will tell you which of your medicines you can take the morning of surgery (see pages 3 and 4).

## Anesthesia

A team of anesthesia providers will be with you during your surgery to keep you comfortable. They will also manage your breathing, heart rate, blood pressure, and any medical issues that might arise.

At your Pre-Anesthesia visit, your providers may talk with you about having 1 or more of these types of anesthesia:

- **General anesthesia:** You are unconscious (asleep) and have no awareness of the surgery.
- **Regional anesthesia:** A numbing medicine is injected into a cluster of nerves, so you do not have feeling in a large area of your body. You may also be given medicine to relax you or help you sleep.
- **Monitored anesthesia care (MAC):** MAC drugs are given through a vein in your arm (*intravenously*). You may receive *sedation* (medicine to make you relax), but you may be awake during your

procedure. You may also be given a *local anesthetic*, which numbs the area where the procedure will be done. With MAC, you may be drowsy, very sleepy, or fall into a deep sleep.

During your Pre-Anesthesia visit, please tell your provider if you want to talk with an anesthesiologist about any special concerns.

## Before Your Surgery

Unless your doctor gave you instructions for a bowel cleanse, on the day and evening before your surgery, eat normally and take your medicines as usual.

Starting at midnight before your surgery day, follow our *fasting guidelines*.

### Fasting Guidelines

**You MUST follow our fasting guidelines before your surgery.** For your safety, if you do not follow our fasting guidelines, we may need to reschedule your surgery for another day.

These guidelines are important. They lower your risk of vomiting and inhaling stomach contents into your lungs during surgery.

Some patients may be able to drink liquids after midnight the night before their surgery. This depends on the type of surgery you are having. Your provider will explain the guidelines that you need to follow.

Follow these guidelines about not eating or drinking before surgery:

**For ALL patients:**

- Do **NOT** eat after midnight.
- Do **NOT** drink alcohol after midnight.

**If you were told NOT to drink clear liquids after midnight:**

- Take your medicines in the morning as instructed by your provider. Take them with no more than 2 ounces (4 tablespoons) of water.

**If you are on a Clinical Care Pathway for your surgery:**

- Follow your surgeon's instructions on when to drink your apple juice. Most patients drink 8 ounces before midnight, and 8 ounces when they get to the parking garage at UWMC.

**If you were told you MAY drink clear liquids after midnight:**

- You may drink liquids such as water; apple, cranberry, or other clear juices without pulp; Gatorade; and clear tea.

- Do **not** drink orange juice, coffee or tea with cream or milk, or other liquids that are not clear.
- Starting 2 hours before you arrive for your surgery, do **not** drink anything. If you need to take medicines during those 2 hours, take them with no more than 2 ounces (4 tablespoons) of water.

## Shower with CHG Soap

**Shower or bathe both the night before and the morning of surgery**. Wash with a special soap called *Chlorhexidine gluconate* (CHG).

You can buy CHG at most large drugstores. You may use either a 2% or a 4% solution. A common brand is *Hibiclens*, but you may use any brand.

For your showers the night before and the morning of your surgery:

1. If you want to wash your face and hair, do it first using your regular soap and shampoo. Do **NOT** use CHG on your face or hair.
2. After you wash your face and hair, step away from the shower or turn the water off.
3. Use a wet washcloth to apply lots of CHG soap from your neck to your toes. Add more soap as needed to get your whole body clean, especially the part of your body where you will have surgery.
4. Let the CHG soap stay on your skin for 1 full minute. After 1 minute, turn the shower on again and rinse well.
5. Pat your skin dry with a clean towel. Put on **clean** clothes.
6. After your morning shower or bath, do **NOT** put on makeup, deodorant, lotions, hair products, fragrances, or jewelry.

## Shaving

- To lower the risk of infection, do **not** shave any part of your body that you do not already shave every day.
- If you normally shave near your surgical site, **DO NOT** shave that area for 2 days (48 hours) before the morning of your surgery.

## Parking and Directions

Parking at the hospital is validated for a reduced rate. See pages 14 and 15 for maps and directions to parking areas. For more information on:

- UW Campus parking and fees, call 206.685.1543
- Hospital parking, call 206.598.5275
- Driving directions, visit *www.washington.edu/ admin/commuterservices/get_to_uw/ visitors/index.php*

## Your Ride Home

If you are leaving the hospital the same day that you have surgery, **you cannot drive a car or ride a bus or taxi by yourself**.

- A responsible adult (*escort*) **must** take you home or to your recovery facility. This person must also help you settle in and make sure you are safe and comfortable.
- If your escort is not present when you check in, we will ask for their name and phone number. **If you do not have an escort, your surgery may be cancelled.**
- Your escort must be at the hospital within 30 minutes of your discharge.

## Coming to the Hospital for Surgery

- Do **not** use any makeup, deodorant, lotion, hair products, or scents.
- Wear loose clothing that will be easy to take off and comfortable to wear home.
- Please do not bring valuables with you.
- Remove all jewelry and body piercings.

### What to Bring with You

- A list of your medicines and the doses of each one. Do not bring the actual medicines unless you were told to do so.
- A photo ID, your health and pharmacy insurance cards, and method of payment (co-pay) for any discharge medicines you may need.
- A copy of your healthcare directive and/or durable power of attorney for healthcare, so they can be placed in your medical record.
- Your L&I claim number, if you have one.
- Your CPAP machine if you have sleep apnea and use the machine at night to help you breathe.
- A book to read or project to do while waiting for your surgery to start.

### Checking In

On the day of your surgery, come to the location that is checked on page 2 of this booklet.

Most times, we ask you to come in 1½ to 2 hours before your surgery. This gives us time to prepare you for your surgery. During this time:

- You will sign admission forms.
- We will check for any changes in your health.
- We will tell you about any changes that might affect your surgery start time.

**Female Patients:**

You may receive information about a urine pregnancy test before surgery. Tell your nurse or an anesthesia staff person if you want to be tested.

## Getting Ready for Surgery

Many patients will be in the surgery "prep" area getting ready for their surgery. In a private space, we will ask you to remove your clothes, including underwear. You will put on a hospital gown.

You will need to remove glasses, contact lenses, and hearing aids. You may be asked to remove dentures if you wear them. Please bring cases to store these items, if you have them.


You will meet the nurses, the surgical team, and the anesthesia team who will care for you during your surgery. You will be able to ask them any questions you have about your care.

To reduce your risk of infection, you will be covered with a heating blanket to keep your body warm while you wait to go into the operating room. Ask for a heating blanket if you do not receive one.

## Your Support Person

An adult support person is welcome to be with you during your "prep" time.

- Please make sure that your support person is healthy.
- Your support person may be asked to step out of the prep area, if needed.
- When you are taken to surgery, your support person may wait in the waiting room. They may want to bring something to read while they wait, or a laptop computer or other electronic device to use. Wireless internet access is available in most areas of the hospital.




*A surgeon writing their initials on a patient's surgery site.*

- We cannot provide child care. If you must bring a child age 17 or under to the hospital, please bring an adult to be with them at all times in the waiting room and other areas of the hospital.

## Surgical Site Marking

We are committed to making sure you receive high-quality and safe care. While you are here, you or your family will be asked such questions as:

- What is your name?
- What is your date of birth?
- What surgery are you having done?

Please do not be alarmed by these questions. We know who you are. We ask some or all of these questions over and over again for your own safety.

Your doctor will check your medical record and talk with you or a family member to confirm your surgery or procedure site. Most times when you have surgery or a procedure, your doctor will mark the site in pen to help ensure your safety.

If your surgical site needs to be marked, your surgeon will mark the site with their initials. Special care is taken if you are having surgery or a procedure on the right or left side of your body. **Please do not mark yourself or write anything on your body.**

If your site does not need to be marked, we will ask you to confirm what surgery or procedure you are having.

## Starting Your IV

Before your surgery begins, we will start an *intravenous* line (IV). An IV is a small needle and thin tube that are used to give you medicine and fluids during surgery. You might also be given medicine through your IV to help you relax before you go into surgery.

We will first apply numbing medicine to your skin where the IV will be placed. Most times, this is on your hand or arm.

## After Surgery

### Recovery Room

You will be taken to the recovery room after your surgery. The recovery room is also called the Post-Anesthesia Care Unit (PACU).



*With PCA, you control the amount of pain medicine you receive.*

Right after your surgery, our first priority is to give you the care you need. We want to make sure you are safe as you wake up from anesthesia, and that you receive treatment for pain as needed.

Most patients are in the recovery room for 1 to 2 hours after their surgery.

## Visitors

After we have given you the care you need right after surgery, we will tell your loved ones that you can receive visitors.

- Most times, your loved ones will be able to visit you in the PACU, if you wish. There is limited space in the PACU area, so you may have only 1 adult visitor at a time.
- We ask that all visitors be healthy. A visitor who has an infection, even " just" a cold, could affect your recovery or treatment.
- *If you will be admitted to one of our oncology units after surgery:* We do a health screen of all visitors when they arrive at the unit. If they have any symptoms of illness, we may ask them to come back when they are well.

## Monitoring

As you recover from surgery, a nurse will check your breathing, heart rate, and blood pressure often. Your nurse will help you with any nausea or pain you may feel. It is important for you to be comfortable.

## Pain Control

Be sure to ask your nurse for pain medicine before your pain gets too bad. Your nurse will ask you to rate your pain on a scale from 0 to 10, where 0 is no pain and 10 is the worst pain. You may receive pain relief by:

- Mouth (pills, capsules, or liquid)
- Medicine put into your IV tube

If you are staying overnight in the hospital, you may also receive:

- Pain medicine given through a small tube in your back (*epidural*)
- Patient-controlled analgesia (PCA)

### About Patient-controlled Analgesia

A PCA machine puts a dose of pain medicine into your IV tube when **you** push a button. With PCA, you do not have to wait for a nurse. You are in control of your pain relief.

Your doctors will prescribe the best dose of medicine for you. You will **not** become addicted to these medicines if you use the PCA as instructed.

**WARNING:** For your safety, **only you** should push the button on your PCA. Do **NOT** let your visitors push the PCA button.

## Discharge on the Same Day as Your Surgery

If you are discharged from the hospital on the same day as your surgery, and you received sedation or anesthesia:

- You **must** have a responsible adult escort you home or to the place where you will stay while you recover from surgery.
- You **cannot** drive yourself.
- You **cannot** take a taxi or bus by yourself.

If you have not arranged for an adult or approved transportation (such as Cabulance) to escort you when you are discharged from the hospital, we may cancel your procedure. Your escort must help you get into your home or place of recovery and help you settle in.

### The First 24 Hours

- We strongly advise that a responsible adult stay with you for 24 hours after discharge. This adult should be able to help take care of you at home or in your place of recovery. This is for your safety, in case you have any problems and need extra care after your surgery. **If you choose not to follow this advice, UWMC is not responsible for your safety.**
- You can expect to have some pain and maybe some nausea after surgery. You may also be sleepy for the rest of the day.
- For 24 hours after having anesthesia, **DO NOT**:
  - Drive
  - Drink alcohol
  - Travel alone
  - Use machinery
  - Sign any legal papers
  - Be responsible for children, pets, or an adult who needs care
- Before you leave the hospital, we will give you:
  - Information about how to care for yourself at home.
  - A number to call to set up your follow-up visit, if this is not scheduled already.

## If You Stay Overnight in the Hospital After Surgery

- You may need to wear a hospital gown.
- We will do everything we can to protect your modesty while keeping you safe. Your safety is our first priority.
- You may have *sequential compression devices* (SCDs) on your lower legs while you are in bed. These wraps help prevent blood clots.



*SCDs inflate from time to time to help blood circulate in your legs.*

- To keep you from falling, we may use:
  - An alarm that tells us when you are getting out of bed
  - Mats on the floor near your bed
  - A belt around your waist when you get out of bed and when you walk
  - A staff member to stay nearby when you use the toilet or commode
- Your ability to do things by yourself may change day to day. This means that we may also need to change the things we do to keep you safe.
- You may be connected to tubes and machines.
- Staff will check how you are feeling many times a day.
- We will ask you to take part in tests.

### Risk of Falling

While you are in the hospital, your risk of falling is higher. This is because:

- You are in a new place.

- You may be weak and tired from changes in your health or illness.
- You may feel dizzy, lightheaded, or confused after surgery or because of your illness.
- Some medicines can affect your ability to think clearly.
- Some medicines can cause an urgent need to urinate (pee).
- Your bathroom habits are different in the hospital than they are at home.
- Some medicines can affect your muscle strength.
- You may have swollen legs.
- You may move more slowly or shuffle your feet after surgery.
- You may not sleep well away from home.
- Tubes and machines can get in the way of moving easily.

Please ask your nurse if you have any questions or concerns about how we help keep you from falling while you are staying in the hospital.

## Helpful Phone Numbers

You may find these phone numbers helpful. If you are using a phone inside the hospital, press only the last 5 digits of numbers that start with 598. (For example, to reach Admitting from a hospital phone, press 8.4310.)

**Admitting**........ 206.598.4310

**Bills**
Financial counseling ........ 206.598.4320
Doctor fees (UW Physicians) ........ 206.543.8606
UWMC billing ........ 206.598.1950

**Emergency Medicine Service**
(Emergency Room or ER) ........ 206.598.4000

**Health Information Resource Center**........ 206.598.7960

**Interpreter Services**........ 206.598.4425
*TTY* ........ 800.833.6384

**Lost and Found**........ 206.598.4909

**Operating Room**........ 206.598.4270

**Patient Relations**........ 206.598.8382

**Pavilion Surgery Center** ........ 206.598.4214

**Pre-Anesthesia Clinic** ........ 206.598.5053

**Roosevelt Ambulatory Surgery Center**........ 206.598.0900

**Social Work and Care Coordination**
**Housing Services** ........................................................ 206.598.4170

> **Your surgical clinic will also give you numbers to call if you have questions or concerns after surgery.**

## Locations and Parking


### UWMC - Montlake

UWMC - Montlake is at the south end of the UW campus. The address is 1959 N.E. Pacific St., Seattle. You may park in one of these garages:

- **Triangle Parking Garage** (across N.E. Pacific St. from the hospital)
- **Surgery Pavilion Parking Garage** (at the east end of the hospital)

### UWMC - Roosevelt

UWMC - Roosevelt is about 1 mile northwest of UWMC - Montlake, at 4245 Roosevelt Way N.E., Seattle. The parking garage is under the building.




*Stars show the entrances to the Triangle Garage and the Surgery Pavilion Parking Garage.*



*UWMC - Montlake campus is east of Interstate 5 and north of State Route 520.*

## Driving Directions

**UWMC - Montlake Campus**, 1959 N.E. Pacific St., Seattle, WA 98195

- From Interstate 5:
  - Take Exit 168B (Bellevue, State Route 520) heading east.
  - Take the Montlake Blvd. exit.
  - Follow the signs to University of Washington Medical Center.
- From Interstate 405:
  - Take Exit 14 (to Seattle via State Route 520) heading west.
  - Take the Montlake Blvd. exit.
  - Follow the signs to University of Washington Medical Center.

**UWMC - Roosevelt**, 4245 Roosevelt Way N.E., Seattle, WA 98105

- From Interstate 5:
  - Take the N.E. 45th St. exit (Exit 169) and go east on N.E. 45th St.
  - Turn right heading south on Roosevelt Way N.E. Go 2½ blocks.
  - UWMC - Roosevelt is on the right.




### Questions?

We want to partner with you to give you our best care. Patients who are involved in their care have better results and fewer problems.

Your questions are important. Ask your caregiver any questions you may have about the care you receive. If you have a concern, tell a staff member or call UWMC's Patient Relations at 206.598.8382.


© University of Washington Medical Center


Published PFES: 2003, 2010, 2013, 2015, 2016, 2017, 2018, 2019, 2020
Clinician Review: 07/2020
Reprints on Health Online: https://healthonline.washington.edu